የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

አሥራአምስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፮
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፫ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th Year No. 46
ADDIS ABABA 30th June, 2009


<u>ማውጫ</u>


አዋጅ ቁጥር ፮፻፴፱/፪ሺ፩ ዓ.ም

**የፍትሐብሔር ሕግ /እንደተሻሻለ/ አዋጅ** … ገጽ ፬ሺ፯፻፵፰


**CONTENTS**


**Proclamation No. 639/2009**

Civil Code (Amendment) Proclamation ………………… Page 4748


## <u>አዋጅ ቁጥር ፮፻፴፱/፪ሺ፩</u>

## <u>የፍትሐብሔር ሕግን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ</u>

የማይንቀሳቀስ ንብረትን በመያዣነት ለመስጠት ስለ ሚደረግ ውል በፍትሐብሔር ሕግ የተደነገገው ሥርዓት የባንኮችና የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ዋነኛ የዕለት ተዕለት ተግባር በሆነው የብድር አቅርቦት አገለግሎት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድር ሆኖ በመገኘቱ፣

ባንኮችና አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ሲከተሉት በቆየው አሠራር መሠረት ያደረጓቸው የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ ውሎች በፍትሐብሔር ሕጉ በተደነገገው ሥርዓት መሠረት ሥልጣን ባለው አዋዋይ ፊት የተፈረሙ ባለመሆናቸው እንዲፈርሱ ቢደረግ የሰጧቸውን ብድሮች በአብዛኛው ዋስትና የለሽ በማድረግ በባንኮቹና በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማቱ ህልውናና በጠቅላላው በሀገሪቱ ኢኮ ኖሚ ላይ ከፍ ያለ ጉዳት የሚያስከትል በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብ ሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ /፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የፍትሐብሔር ሕግ /እንደተሻሻለ/ አዋጅ ቁጥር ፮፻፴፱/፪ሺ፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ፪. <u>ማሻሻያ</u>

በ፲፱፻፶፪ቱ የኢትዮጵያ ፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር ፩ሺ፯፻፳፫ ሥር የሚከተለው አዲስ ንዑስ ቁጥር /፫/ ተጨምሯል፤

## <u>PROCLAMATION NO. 639/2009</u>

## <u>A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE AMENDMENT OF THE CIVIL CODE</u>

**WHEREAS,** the formality provided under the Civil Code for the conclusion of mortgage contracts is exerting negative impact on the efficiency of loan provision service which is the day-to day activity of banks and micro-financing institutions;

**WHEREAS,** the invalidation of existing contracts of mortgage concluded under the prevailing practices of banks and micro-financing institutions for not being notarized, as provided for by the Civil Code, may leave most of the existing loans unsecured with a serious threat to the existence of the banks and the micro-financing institutions and to the country's overall economy;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

### 1. <u>Short Title</u>

This Proclamation may be cited as the "Civil Code As Amended Proclamation No. 639/2009".

### 2. <u>Amendment</u>

The following new sub-article (3) is added under Article 1723 of the 1960 Ethiopian Civil Code.

"፫/ የዚህ ቁጥር ንዑስ ቁጥር /፩/ ድንጋጌ ቢኖርም ለባንክ ወይም ለአነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ብድር መያዣነት የተሰጠ የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከት ውል በፍርድ ቤት መዝገብ ወይም ሥልጣን በተሰጠው አዋዋይ ፊት መፈረም አያስፈልገውም።"

## ፫. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

፩/ ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት ለባንክ ወይም ለአነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ብድር መያዣነት የተሰጠ የማይንቀሳቀስ ንብረትን በሚመለከት የተደረገ ውል የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር ፲፯፻፳፫ ድንጋጌን መሠረት በማድረግ በፍርድ ቤት መዝገብ ወይም ሥልጣን በተሰጠው አዋዋይ ፊት አልተደረገም በሚል ምክንያት ተቃውሞ ሊቀርብበት አይችልም።

፪/ ለባንክ ወይም ለአነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ብድር መያዣነት የተሰጠ የማይንቀሳቀስ ንብረትን በሚመለከት የተደረገ ውል በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር ፲፯፻፳፫ መሠረት በፍርድ ቤት መዝገብ ወይም ሥልጣን በተሰጠው አዋዋይ ፊት አልተደረገም በሚል ተፈጻሚነት እንዳይኖረው ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በማናቸውም ፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ አይጸናም። ይህ አዋጅ በሚጸናበት ጊዜ በማናቸውም ፍርድ ቤት በመታየት ላይ ያለ ተመሳሳይ ክርክርም ይቋረጣል።

## ፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሰኔ ፳፫ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

"3/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, a contract of mortgage concluded to provide security to a loan extended by a bank or a micro-financing institution may not require to be registered by a court or a notary."

## 3. <u>Transitory Provisions</u>

1/ The validity of any contract of mortgage concluded, prior to the effective date of this Proclamation, to provide security to a loan extended by a bank or a micro-financing institution, may not be challenged for not being registered by a court or notary in accordance with Article 1723 of the Civil Code.

2/ Any court decision, rendered prior to the effective date of this Proclamation, to invalidate a contract of mortgage concluded to provide security to a loan extended by a bank or a micro-financing institution, for not being registered by a court or notary in accordance with Article 1723 of the Civil Code shall have no effect. Any such case pending before any court as of the effective date of this Proclamation shall also be terminated.

## 4. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 30th day of June, 2009**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**